# JK ፖሊሲ- የተማሪ ዲሲፕሊን

I. መግቢያ

A. ከተለያየ የዘር ግንድ ሐረግ ለመጣው ለእኛ ማህበረሰብ፣ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያላቸው ዜጎች እንዲሆኑ ለሁሉም ተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን ዕውቀት እና ክህሎት እኩል የመስጠት ተልዕኮ ያለውን የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ("ዲስትሪክት") ተልዕኮ የትምህርት ቦርዱ ይደግፈዋል። ተማሪዎች ገንቢ እና ተጠያቂነት ባለበት የትምህርት ቤት ቅንጅት ውስጥ ክህሎቶቻቸውን፣ ዕውቀታቸውን እና ችሎታቻቸውን እንዲያጎለብቱ ዕድሉ ሊሰጣቸው ይገባል። እንደየሁኔታው እንዲጣጣም ተደርጎ የተቀረጸ የትምህርት መርሃ ግብር፣ የማስተማር ስልት እና ግምገማ የእኛን ከተለያየ ሁኔታ የተውጣጡ ተማሪዎቻችንን ፍላጎት ለማሟላት ተብሎ የተዘጋጀ የተዋጣለት እና በማስተማር ሂደቱ አሳታፊ የሆነ ትምህርት ተማሪዎች ማግኘት አለባቸው። ተማሪዎች ካላስፈላጊ ሁከት የጸዳ ደሕንነቱ አስተማማኝ በሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ የመማር መብት አላቸው። አዎንታዊ የሆነ የትምህርት ቤት ድባብ ለመፍጠር እና ጠብቆ ለማቆየት በተዋጣለት የዲሲፕሊን መርሃግብር የሚቃኝ፣ ተገቢነት ያለው የተማሪ ስነምግባር መኖርን አስፈላጊነት ቦርዱ ያምንበታል። ይህ የተማሪዎች፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ወላጆች እና የማህበረሰቡ የጋራ ኃላፊነት ነው።

II. ዓላማ

A. በተማሪ ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ ግቡ የተማሪዎችን አካዳሚያዊ ውጤት እና የትምህርት ቤት ስኬት ላይ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ በሚችሉበት መንገድ ጸባይ እንዲያሳዩ ማስተማር እና ተማሪዎች እና ሠራተኞች ኃላፊነት የተሞሉበት እና እርስ በእርስ የሚከባበሩበት የትምህርት ቤት ድባብ እንዲፈጠር ለማገዝ ነው።

B. የዚህ ፖሊሲ ዓላማ የሚከተሉትን ያሟላ የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን እንዲኖር ማገዝ ነው፥

i. ደሕንነቱ የተጠበቀ በስርዓት የተደራጁ ማህበረሰቦች፣

ii. በዲስትሪክቱ ውስጥ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥ ወጥነት ያለው አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ፣

iii. ከተማሪ ባሕሪ የሚጠበቀውን በግልጽ የሚያስቀምጥ እና መልዕክቱን የሚያስተላልፍ፣

iv. ለትምህርት ቤት ዲሲፕሊን ከሠራተኞች የሚጠበቀውን እና ያለባቸውን ኃላፊነት በግልጽ የሚያስቀምጥ እና መልዕክቱን የሚያስተላልፍ፣

v. የተማሪው ፍላጎቶችን፣ በባሕሪው በቀጥታ የተጎዱ ሰዎችን ፍላጎት፣ እና እንዲሁም የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ፍላጎት ሚዛን የሚጠብቅ፣

vi. በዘረ ሐረግ፣ በጎሳ እና የባሕል ቡድኖች እንዲሁም በሌሎች ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው መደቦች (ጾታ፣ የቆዳ ቀለም፣ የብሔር/የሃገር ምንጭ፣ የትውልድ ሐረግ፣ ሃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ እና የጾታ ምንነት) እኩልነት መኖሩን የሚያረጋግጥ።

III. አጠቃላይ መርሆዎች

A. የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን አንድ የስነምግባር ጉደለት ከመፈጠሩ በፊት መከላከል ቢችል ይመረጣል፣ ነገር ግን ከተፈጠረ ደግሞ በተሳካ ሁኔታ ጉድለቱን ማረቅ ያስፈልጋል።

B. ሁሉም የትምህርት ቤት ሠራተኞች እና ባለሙያዎች ከተማሪዎች ጋር አዎንታዊ ግንኙነት ሲመሰርቱ እና በተማሪዎቹ ሕይወት እና በትምህርታቸው ላይ በንቃት ተሳትፎ ሲኖራቸው የትምህርት ቤት ደሕንነት እና አካዳሚያዊ ስኬት ተመስርቶ ይበልጥ እየተጠናከረ ይሄዳል።

C. የተዋጣለት የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን አወሳሰድ ተማሪዎች በትምህርት ላይ የሚያጠፉትን ጊዜ በመጨመር ተማሪዎች ሁከት በመፍጠር ወይም በስነምግባር ጉድለት ምክንያት ከመማሪያ ክፍሎች የሚወገዱበትን ጊዜ ይቀንሳል።

D. የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን ምክንያታዊ፣ ጊዜውን የጠበቀ፣ ፍትሓዊ፣ ከዕድሜ ጋር ተመጣጣኝ መሆን እና ተማሪው ካሳየው የስነምግባር ጉድለት ከባድነት ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት። ትርጉም ያለው አስተምህሮ እና አመራር የሚሰጥ የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን ተማሪዎችን ከስሕተቶቻቸው እንዲማሩ እና ለማህበረሰቡ በጎ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ እንዲሁም ተማሪዎች መልሰው ትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ዕድል ይሰጣል።

E. ውጤታማ ዲሲፕሊን አወሳሰድ ወጥነት እና ውጤታማ የመማሪያ ክፍል አስተዳደር ላይ ይመሰረታል እንዲሁም በአዎንታዊ የትምህርት ቤት ድባብ ይደገፋል። አብዛኛዎቹ የሚወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ደረጃ በመምህራን የሚወሰዱ እርምጃዎች ቢሆኑም በዚህ ደረጃ እልባት ሊሰጣቸው ያልቻሉ የስነምግባር ጉድለቶች እንደ ተፈጠረው ሁኔታ አስገዳጅነት የሚወሰን ሆኖ ይበልጥ የተጠና እና ትኩረት ያለው ማስታረቂያ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል።

F. ዲስትሪክቱ ከተለያየ ሁኔታ የተሰባሰበ ማህበረሰብን ያገለግላል። ሁሉንም ተማሪዎች ለማገልገል እና በየጊዜው ልዩነቱ እየጨመረ የሚመጣ ማህበረሰብ አባል እንዲሆኑ አድርጎ ለማዘጋጀት ይቻል ዘንድ ትምህርት ቤቶች እና ሠራተኞች የመቻቻል የባሕል ብቃት ሊገነቡ ይገባል። ማናቸውም ከስኬት ሊያግድ የሚችል በድርጅት ደረጃ የሚፈጸም ዘረኝነትን ሆነ ማናቸውም ዓይነት መድልዎን ለማስወገድ ጥረት ማድረግ አለብን።

G. የዲሲፕሊን እርምጃ የሚያስከትል የተማሪ ስነምግባር ጉድለት በክፍል ውስጥ፣ በት/ቤት ሕንጻዎች፣ ቅጽረ ግቢ ወይም በት/ቤት መኪኖች ውስጥ በትምህርታዊ ወይም ትምህርት ደጋፊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተማሪው የሚያሳየው ስነምግባር ለትምህርት ቤቱ ድባብ እና ለሌሎች ተማሪዎች እና የት/ቤቱ ሠራተኞች ደሕንነት እና ጤና አደጋ ሊያስከትል የሚችል አስጊነት ካለው የተማሪው የስነምግባር ጉድለት የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል።

IV. የፖሊሲው አጠቃላይ መግለጫ

A. የዲስትሪክት የዲሲፕሊን ስርዓት በግል ተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ለማለት ነው፥

i. የስነምግባር ጉድለቱ በግለሰቡ ወይም በግለሰቦቹ፣ በስነምግባር ጉድለቱ ተጠቂ ግለሰብ እና በማህበረሰቡ በአጠቃላይ ያለውን ግንኙነት እንደሚያበላሽ ማወቅ፣

ii. የስነምግባር ጉድለት የፈጸመውን ሰው ከማግለል ይልቅ በተቃራኒው የደረሰውን ጥፋት በማስተካከል እና የነበረውን መልካም ግንኙነት ለመመለስ ዕድል መስጠት፣

iii. ሌሎች ግለሰቦችን ማክበር፣ ራስን መቆጣጠር እና ተነሳሽነትን እንዲያጎለብቱ ለማገዝ የግል ኃላፊነትን ማደርጀት፣

B. የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰዶች በሚከተሉት መርሆች መመራት አለባቸው፥

i. ችግር ሊኖርባቸው የሚችሉ ተማሪዎች ችግሩ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በጊዜ ችግራቸውን በማወቅ እና በመገምገም ላይ መሳተፍ፣

ii. ከተማሪው ፍላጎት ጋር የሚዛመድ ማስታረቂያ እርምጃ ለመውሰድ ችግር ፈቺ አካሄድን መጠቀም፣

iii. ጊዜውን የጠበቀ ክትትል እና ግብረ መልስ አሰጣጥ መኖሩን ማረጋገጥ

iv. ከታማኝነት ጋር ሳይንሳዊ በጥናትና ምርምር ላይ የተመረኮዘ የማስታረቂያ እርምጃ መውሰድ።

C. ሶስት ዓይነት የማስታረቂያ እርምጃ አወሳሰድ ስትራቴጂዎች አሉ፥ አስተዳደራዊ፣ መልሶ ማስተካከያ እና በክህሎት ላይ የተመሰረተ/ቴራፓቲክ። መምህራን እና አስተዳዳሪዎች በተለይ ለ2ኛ ወይም ለ3ኛ ጊዜ በሚፈጸሙ ጥፋቶች ላይ የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ወይም በርካታ ስትራቴጂዎችን በአንድ ጊዜ በአንድ ላይ መጠቀምን ከግምት ማስገባት አለባቸው።

D. የተማሪን የስነምግባር ጉድለት በትምህርት ቤት ላይ ያሉ ግብዓቶችን በተቻለ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለማስተካከል፣ እና አዎንታዊ የትምህርት ቤት ድባብ እንዲበለጽግ አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን ተማሪዎች እንዲማሩ እና አሉታዊ ባሕሪያትን ለማስወገድ ዲስትሪክቱ ሁሉንም የሚቻል ጥረት ያደርጋል።

E. የዲስትሪክት ሠራተኞች ዲሲፕሊናዊ እርምጃዎችን በሚወስዱበት ወቅት ሁሉንም ተገቢነት ያላቸው ፌደራል እና ስቴት ሕጎች እና የከተማ መመሪያዎች፣ እንዲሁም ተዛማጅነት ያላቸው የቦርዱ ፖሊሲዎች እና የአፈጻጸም መመሪያዎች ማክበር አለባቸው።

F. እያንዳንዱ ተማሪ ይህን ፖሊሲ እና አብረውት የሚሄዱ አፈጻጸም መመሪያዎች እንዲያከብር ይጠበቅበታል።

G. ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ የስነምግባር መመዘኛ ደረጃዎችን አሟልተው እንዲገኙ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ መምህራን እና ሠራተኞች ለተማሪዎቹ በማስተማር፣ ሞዴል በመሆን፣ ጠባያቸውን በመቆጣጠር እና አስፈላጊ ሲሆን የጸባይ ጉድለትን በማረም እነዚህ ደረጃዎች ተጠብቀው እንዲቆዩ ያደርጋሉ። ተማሪዎች ለትምህርት ቤታቸው እና ለመማሪያ ክፍሎቻቸው በሚዘጋጁ የዲሲፕሊን ደንቦች አቀራረጽ ወቅት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።

H. ትምህርት ቤቶች የስቴት ሕጎች፣ የአካባቢ ሕጎችን እና የግዴታ የሆኑ ሪፖርት የማቅረብ ሕጎችን ሳይጣረሱ በተቻለ መጠን ተገቢነት እስካለው ድረስ ከትምህርት ቤት ውጪ ከሚደረግ እገዳ፣ ከትምህርት ገበታ ከማባረር እና ተማሪዎችን ለሕግ አስከባሪ አካላት አሳልፎ ከመስጠት መቆጠብ አለባቸው። በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚፈጠር የስነምግባር ጉድለት እርምጃ ለመውሰድ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች እና የወንጀለኛ መቅጫ የፍትሕ ስርዓቶች በጣም ባነሰ ድግምግሞሽ ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቦርዱ ግብ ነው።

I. የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ አሰራሮች ለሁሉም ተማሪዎች እኩል ተፈጻሚ መሆን መቻላቸውን እና ወጥነትን፣ ፍትሓዊነትን፣ ተመሳሳይነትን ጠብቀው በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በብሔር/ሃገር ምንጭ፣ የትውልድ ሃረግ፣ ጾታ፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ ዕድሜ ወይም አካል ጉዳተኝነት ተመርኩዘው መድልዎ ሳይፈጸም ተግባራዊ ለመሆን ስለመቻላቸው ዋስትና መስጠት አለባቸው።

J. ይህ ፖሊሲ እና አብረውት የሚሄዱ አፈጻጸም መመሪያዎች በትምህርት ቤት ዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ ላይ ዲስትሪክቱ የዘር እና የጎሳ ልዩነት ወይም ሌላ ማናቸውም ዓይነት ልዩ ጥበቃ በሚደረግላቸው መደቦች ላይ መድልዎ እንዳይፈጸም እና ባሕሪን የትምህርት ቤት ድባብን እና አካዳሚያዊ ስኬትን ለሁሉም ተማሪዎች ለማሻሻል እንዲችል እንዲያግዙት ተብለው የተዘጋጁ ናቸው።

K. ትክክለኛ የሆነ እና የተሟላ የውሂብ (ዳታ) ስብሰባ ውጤታማ የሆነ የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን ፖሊሲን በተግባር ላይ ለማዋል አስፈላጊ ነው። የሚሰበሰበው መረጃ ችግሮችን ለይቶ ለማወቅ፣ መፍትሔዎችን ለማበጀት እና የመሻሻል ሂደቶችን ለመከታተል ያግዛል።

L. የትምህርት ቦርዱ በ C.R.S በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለዲስትሪክቱ ይህን ፖሊሲ እና አብረውት የሚሄዱ አሰራር መመሪያዎች/ ደንቦች ለደሕንነቱ አስተማማኝ የሆነ ትምህርት ቤት መፈጠር ተገቢነት አለው በማለት አዘጋጅቶ አጽድቋል። 22-32-109.1. ትምህርት ቤቶች ከዚህ ፖሊሲ፣ አብረውት ከሚሄዱ ደንቦች ወይም ሌሎች የቦርድ ፖሊሲዎች ጋር የማይጣረሱ እስከሆነ ድረስ እና በሱፐር ኢንቴንደንቱ ወይም ወኪሉ እስከጸደቀላቸው ድረስ የየራሳቸውን የስነምግባር ደንብ ማዘጋጀት ይችላሉ።

M. ዲስትሪክቱ ይህን ፖሊሲ በዲስትሪክቱ እና በእያንዳንዱ ትምህርትቤት የድር ጣቢያ (ዌብሳይት) ላይ ይለጥፋል። የዚህ ፖሊሲ ቅጂ፣ አብረውት የሚሄዱ የአሰራር ስርዓቶች/ደንቦች እና የትምህርት ቤት ደንቦች፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አስተዳደር ቢሮ በስፓኒሽ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ መቀመጥ አለበት። የዚህ ፖሊሲ ቅጂ፣ አብረውት የሚሄዱ የአሰራር ስርዓቶች/ደንቦች እና የትምህርት ቤት ደንቦች፣ ጥያቄው ሲቀርብ ለእያንዳንዱ ተማሪ እና ለወላጅ/አሳዳጊ መሰጠት

ያለበት ሲሆን፣ በተጨማሪ ጥያቄው ከቀረበ፣ ወላጅ/አሳዳጊ በሚገባው ቋንቋ ፖሊሲው በፍጥነት ተተርጉሞ እንዲሰጠው ይደረጋል።

N. ሱፐር ኢንቴንዳንቱ ወይም ወኪሉ እነዚህን አፈጻጸሞች ለፖሊሲው በሥራ ላይ መዋል በሚመች መልኩ ሊያዘጋጃቸው ይችላል።

እንዲጣጣም ተደርጎ የተዘጋጀው ጃንዋሪ 14፣ 1994
የተሻሻለው ሴፕቴምበር 5፣ 1996
የተሻሻለው ጁን 18፣ 2000
የተሻሻለው ጁን 21፣ 2001
የተሻሻለው ኖቬምበር 15፣ 2001
የተሻሻለው ዲሴምበር 18፣ 2003
የተሻሻለው ኦገስት 21፣ 2008

ሕጋዊ ዋቢዎች፥ C.R.S. 18-12-105.5
C.R.S. 18-18-102
C.R.S. 18-18-406
C.R.S. 18-18-407(2)
C.R.S. 22-32-102(1)(W)
C.R.S. 22-32-209
C.R.S. 22-32-110(2)(3)(4)
C.R.S. 22-32-126
C.R.S. 22-33-105
C.R.S. 22-32-106
C.R.S. 22-32-109.a(2)(a)X
20 USC 88921
C.R.S. 22-32-109.1 (የስነምግባር እና የዲሲፕሊን ኮድ እንዲሁም ከክፍል መወገድ ዲሲፕሊናዊ እርምጃን ጨምሮ ደሕንነት የተጠበቀ የትምህርት ቤት ዕቅድ አወጣጥ እና አፈጻጸም)